# በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ
# 17ኛ መደበኛ አመታዊ ጉባኤውን አካሄደ

በጀርመን የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ 17ኛ መደባዊ አመታዊ ጉባኤውን በፍራንክፈርት ከተማ ጥቅምት 18 ቀን 2004 ዓ.ም.(29.10 2011) ከተለያዩ ከተሞች በመጡ በርካታ አባላቱ በተገኙበት በተሳካና በደመቀ ሁኔታ መጠናቀቁን ከስፍራው የደረሰን ዜና አመለከተ።

ይህ ጉባዔ በሕሊና ጸሎትና ለዘመናት በተሰኘው የኢሕአፓ የትግል መዝሙር ተከፍቶ፡ ጉባኤውን በማስመልከት የድጋፍ ደብዳቤ ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ የተላከውን የትግል አንድነትና የድጋፍ መግለጫ ከተነበበ በኋላ፣ ድርጅታዊ ሪፖርቶች ቀርበው፣ በዋናነት ምን ማድረግ አለብን በሚለው ዙሪያ ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ማድረግ ብቻ ሳይሆን በምን አይነት ዘዴም የሚለውም በስፋት የተዳሰሰበት ነበር።

በጉባዔ ውይይት ወቅት ቀስቃሽ ጽሁፎችና ግጥሞች፣ አዝናኝና ለትግል አነሳሽ የሆኑ ንባቦች ጭምር ቀርበዋል።

የጉባኤው ተሳታፊዎቹ በርካታ ትምህርታዊ ተመክሮን የቀሰሙበትና የተደሰቱበት፣ ለሌላውም በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ብሩህ ተስፋ ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን ከጉባኤው ፍፃሜ በኋላ የተደረጉ ውይይቶች ግልፅ አድርገዋል።

በመጨረሻም የመዝጊያ ንግግር ተደርጎ ጉባዔው የታለመለትን ሥራ በማጠናቀቅ ተፈጽሟል። ሰፋ ያለና ዝርዝር ሁኔታውን በሚቀጥለው እናቀርባለን።